ደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር

መተዳደሪያ ደንብ

እኛ ከዚህ በኋላ «ማህበሩ» ተብሎ የሚጠራው የደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር መስራቾች ከዚህ በታች በተቀመጡ የስምምነት ቃሎች እና ሁኔታዎች ለመገዛት ፍላጎታችንን በመግለጽ ይህ መተዳደሪያ ደንብ ማህበሩ የሚመራበት እና ስራውን የሚያስተዳድርበት ህጋዊ ገዢ ሰነድ እንዲሆን በአንድ ድምጽ የተስማማን ሲሆን በተጨማሪም ማህበሩ የአነስተኛ ፋይናንስ ስራውን የሚሰራው በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ፣ ከዚህ በኋላ «የንግድ ህግ» ተብሎ የሚጠቀሰው በ1952 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ህግ፣ የአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 እና የብሔራዊ ባንክ በሚያወጣቸው መመሪያዎች በተካተቱ ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል።

ምዕራፍ አንድ

የማህበሩ ሥራዎች

አንቀጽ 1

ሥራውን መስራት ባልተቻለ ጊዜ የትርፍ ክፍፍል ገደቦች

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማህበሩ ካፒታል እና መጠባበቂያ በቂ አይደለም ብሎ ሲወስን እና የተከፈለው የማህበሩ ካፒታል ስራ ለመስራት በቂ አይደለም የሚለው ውሳኔ እስኪነሳ እና ከከፍተኛ ወጪዎች ማህበሩ ሙሉ በሙሉ እስኪያገግም እንዲሁም የተከፈለው ካፒታል እጥረት እስኪወገድ ድረስ በባንኩ ውሳኔ ከሚተላለፈው በስተቀር ማህበሩ በየትኛውም ጊዜ የትርፍ ክፍፍል ማድረግ አይችልም።

አንቀጽ 2

የተወሰኑ ስራዎችን እና እንቅስቃሴዎችን ያለማድረግ ገደብ

1) በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከብድር፣ ከቅድሚያ ተከፋዮች፣ ዕዳዎች ያሉበት ሁኔታ እና ውስንነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማህበሩ ብድር ከመስጠት ወይም ባለዕዳ ከመሆን ጋር በተያያዘ፡-

   ሀ. ከማህበሩ ዳይሬክተሮች ጋር በጋራ ወይም በተናጠል ወይም ከሌላ ከማናቸውም ሰው ጋር፣

   ለ. ማህበሩ እራሱ ወይም ከዳይሬክተሮቹ መሀል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑት ዳይሬክተሮች እንደ ባለቤት፣ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ሸሪኮች፣ ስራ አስኪያጆች፣ ወኪል ወይም አባል ሆነው የሚሳተፉባቸው የንግድ ድርጅቶች፣

   ሐ. ማህበሩ ወይም አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮች ዋስ የሆኗቸው ሰዎች ሁኔታ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሰረት ይወሰናሉ።

2) በማህበሩ እና በማናቸውም ዳይሬክተሮቹ መካከል የተፈጸመ ውል በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ካልተረጋገጠ በስተቀር ዋጋ አይኖረውም።

አንቀጽ 3
ክልከላዎች

ማህበሩ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የጽሁፍ ፈቃድ ወይም ማረጋገጫ ሳያገኝ ከዚህ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አይችልም፡-

1) ከሸያጭ፣ ከማናቸውም ማስተላለፍ፣ ወይም ከሌላ ተቋም ጋር ለመቀላቀል ወይም በሌላ መንገድ ስራውን በሚገድብ መልኩ በማናቸውም ዓይነት መንገድ ለመስራት ማቀድና መስማማት፣

2) ከመደበኛ የስራ እንቅስቃሴው ጋር በተያያዘ ካልሆነ በስተቀር ንብረቱን በሙሉ ወይም በከፊል በማናቸውም መልኩ ኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ውጪ ማስተላለፍ ወይም መስጠት፣

3) የካፒታል ቅነሳ ማድረግ፣

4) የተቋቋመበትን የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻል፣

5) ፈቃድ ያገኘበትን ስም መለወጥ፣

6) ከተፈቀደለት አካባቢ ውጭ መስራት፣

7) የአነስተኛ ፋይናንስ ስራ ለመስራት የተቀበለውን ፈቃድ ስም መቀየር፣

8) ከገንዘብ ተቋማት ጋር ወይም ከሌሎች ተቋማት ጋር በሌላ የስራ ዘርፍ ላይ የማህበሩን መዋለ ንዋይ ስራ ላይ ማዋል የተከለከለ ነው።

ምዕራፍ ሁለት
ባለአክሲዮኖች ካላቸው አክሲዮን ካፒታል ጋር በተያያዘ ያላቸው መብት እና ተጠያቂነት

አንቀጽ 4
የአክሲዮን ካፒታል

1) ማህበሩ አንድ መደብ እና ተመሳሳይ ዋጋ ያላቸው የተመዘገቡ ተራ አክሲዮኖች ይኖሩታል፣

2) አክሲዮኖች በባለአክሲዮኑ ስም ይመዘገባሉ፣

3) ማህበሩ ሳይመዘገቡ የሚተላለፉ አክሲዮኖችን አይሰጥም፣

4) ባለአክሲዮኑ የተፈረመባቸውን አክሲዮኖች ዋጋ አንድ አራተኛ ወይም ከዚያ በላይ የሆነው የአክሲዮኖች ዋጋ ሲከፍል የአክሲዮን ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

5) ባለአክሲዮኖች በባለቤትነት ካያዙት የአክሲዮን ድርሻዎች መጠን ጋር በተያያዘ የሚመነጩ መብቶች፣ግዴታዎች እና ኃላፊነቶች በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ከአንቀጽ 5 እስከ 7 ለተጠቀሱት ድንጋጌዎች ተገዥ ይሆናሉ፣

6) የንግድ ህጉ አንቀጽ 333 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የአክሲዮኖች ዝውውር ወይም ማስተላለፍ በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9 ድንጋጌ መሰረት ይፈጸማል፣

7) ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በጋራ አክሲዮን ሊኖራቸው ይችላል። በዚህ ጊዜ የባለ አክሲዮኖችን መብት ለመጠቀም አንድ ተወካይ ይሾማሉ። ተወካይ ባልተሾመ ጊዜ ከመካከላቸው አንዱ ብቻ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤዎች ላይ መሳተፍ ይችላል፤ከመካከላቸው ለአንዱ በማናቸውም ከአክሲዮኖች ጋር በተያያዘ የትርፍ ክፍፍል ወይም በሌላ ለሚከፈለው ገንዘብ ትክክለኛ ደረሰኝ በአክሲዮኑ ስም ይሰጣል።

አንቀጽ 5
ከአክሲዮኖች ጋር የተያያዙ መብቶች

1) አግባብነት ያላቸው ተፈጻሚ ህጎች እንደተጠበቁ ሆነው ከአክሲዮኖች ጋር የተያያዙ መብቶች ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን፦

ሀ) በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ መገኘት እና የመሳተፍ፤

ለ) በመደበኛ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚጸድቅ እና በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 መሰረት የሚወሰን የትርፍ ክፍፍል ላይ የመሳተፍ፤

ሐ) በእያንዳንዱ ባለአክሲዮን በተዋጣው የካፒታል ድርሻ መጠን የሚሰላ ሆኖ ማህበሩ በሚፈርስበት እና በሚዘጋት ጊዜ በማህበሩ ንብረቶች የተጣራ ገንዘብ ክፍፍል ላይ መሳተፍ፤

መ) አንድ አክሲዮን አንድ ድምጽ ብቻ እንደሚኖረው በመረዳት ድምጽ የመስጠት፤

ሠ) የጠቅላላ ጉባኤዎች ቃለ ጉባኤና የስብሰባ መቆጣጠሪያ ሰነዶችን መመርመር እና የሂሳብ ሚዛን፣ የትርፍ እና ኪሳራ ሂሳብ መግለጫ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የኦዲተሮች የዘገባ ቅጂዎች ግልባጭ የመውሰድ መብት ይሰጣቸዋል።

2) ለካፒታል ጭማሪ አክሲዮኖች በማህበሩ ለሽያጭ በሚመነጨበት እና በሚዘጋጁበት ጊዜ ባለአክሲዮኖች በያዙት የአክሲዮን ድርሻ መጠን ልክ በተነጻጻሪ አዳዲስ አክሲዮኖችን በቅድሚያ የመግዛት መብት የማግኘት መብት ይሰጣቸዋል፤

3) የተከፈሉ አክሲዮኖች ብቻ በንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) እና 1 (ሐ) የተገለጹ መብቶችን ይሰጣሉ።

አንቀጽ 6
የባለአክሲዮኖች መብት እና ተጠያቂነቶች

1) የማህበሩ ባለአክሲዮኖች መብት እና ተጠያቂነቶች በዚህ መተዳደሪያ ደንብ፣ በመመስረቻ ጽሁፍ እና አግባብነት ባላቸው ተፈጻሚ የህግ ድንጋጌዎች ይገዛሉ፤

2) የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ተጠያቂነቶች በያዟቸው የአክሲዮኖች ዋጋ መጠን ብቻ ይወሰናሉ፤

3) የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ለክፍያ በሚጠሩባቸው አክሲዮኖች ዋጋ ተጠያቂ ይሆናሉ። በጥሪው መሰረት ባለአክሲዮኖች ያልከፈሉት ከዚህ በታች በአንቀጽ 7 ላይ በተመለከተው መሰረት እነዚህኑ አክሲዮኖች ሊሸጥ ይችላል፤

4) አንድ አላባ ተቀባይ ለሚደረግለት የክፍያ ጥሪ ተጠያቂ ቢሆንም የአላባ ጊዜው ሲያበቃ ከባለአክሲዮኑ ተመልሶ የአክሲዮኖቹን ዋጋ እንዲከፈለው ካሳ ሊጠይቅ ይችላል።

አንቀጽ 7

የአክሲዮኖች ዋጋ ያለመክፈል ኃላፊነት

1) ባለይዞታዎች፣ የቀድሞ የተላለፈላቸው ሰዎች እና ፈራሚዎች በጋራ እና በተናጠል ሂሳባቸው ተከፍሎ ላልተጠናቀቀ አክሲዮኖች ተጠያቂ ይሆናሉ፣

2) አክሲዮኑን ለሌላ ሰው ያስተላለፈ ማናቸውም ባለአክሲዮን ካስተላለፈበት ዕለት አንስቶ ከሁለት አመታት በኋላ ክፍያ ላልፈጸመባቸው አክሲዮኖች ዋጋ ተጠያቂ መሆኑ ያበቃል፣

3) በማህበሩ የተፈረመን ካፒታል በወቅቱ ያልከፈሉ ባለአክሲዮኖች ባልተከፈለው የካፒታል መጠን ላይ 9% ወለድ ይከፍላሉ፣

4) በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 18 (2) መሰረት የማሳወቂያ ደብዳቤ ከደረሰው በኋላ አንድ ባለአክሲዮን የፈረመባቸውን አክሲዮኖች ዋጋ መክፈል ካልቻለ የንግድ ህግ አንቀጽ 342 ከንዑስ አንቀጽ 4 እስከ 7 የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 8

የባለአክሲዮኖች መዝገብ

1) ማህበሩ በዋና ጽ/ቤቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚፈቅደው ዓይነት የባለአክሲዮኖችን ዝርዝር ከነ ድምጽ የመስጠት መብታቸው የያዘ መዝገብ ይኖረዋል፣

2) መዝገቡ የባለአክሲዮኖችን ስም እና አድራሻ፣ የአክሲዮኖችን ብዛት እና ቁጥር፣የካፒታል መዋጮ መጠን፣ የተከፈለ እና የባለአክሲዮኑ ስም የተመዘገበት ቀን ይጻፍበታል፣

3) መዝገቡ በማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ወይም በዋና የስራው ቦታ ላይ በመደበኛ የስራ ሰዓታት ያለ ክፍያ ለህዝብ ክፍት ይሆናል።

አንቀጽ 9

የአክሲዮን ማስተላለፍ

1) አክሲዮኖች ያለ ምንም ገደብ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ይተላለፋሉ፣

2) በአክሲዮን መዝገብ ያልተመዘገበ ማናቸውም የአክሲዮኖች ዝውውር ውድቅ እና ዋጋ የሌለው ይሆናል፣

3) ማናቸውም የአክሲዮን ዝውውር ወይም መተላለፍ በጽሁፍ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚያጸድቀው ፎርም አይነት ይሆናል፣

4) የጋራ አክሲዮን ይዞታዎች ባለአክሲዮን በሚሞትበት ጊዜ በህይወት ያለው የጋራ አክሲዮኖች ባለይዞታ እና የሚቹ ምትክ ወራሾች በጋራ ከተያዙት አክሲዮኖች በሚመነጩ መብቶች ብቸኛ ተጠቃሚ ሰዎች ይሆናሉ፣

5) የዳይሬክተሮች ቦርድ የአክሲዮኖችን ዝውውርን፣ የተዘዋወሩ አክሲዮኖች ብዛትን፣ የተላለፈለት ሰው ስም፣ አድራሻ እና ዜግነትን በዓመታዊ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ እንዲጸድቅ ያደርጋሉ።

ምዕራፍ ሶስት

የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ

አንቀጽ 10

ጠቅላላ ህጎች

1) የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ከላይ በተጠቀሱት ጠቅላላ ሃላቦች ሳይገድብ የማህበሩ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል በመሆን አግባብነት ባላቸው የአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 እና በንግድ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት የማህበሩን የስራ እንቅስቃሴዎች የመምራት ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ፦

   ሀ) በመመስረቻ ጽሁፍ እና በመተዳደሪያ ደንብ ላይ ማሻሻያ ያደርጋል፣

   ለ) የማህበሩን ዓላማዎች ያሻሽላል፣

   ሐ) ካፒታሉን ከፍ ወይም ዝቅ ያደርጋል፣

   መ) በማህበሩ ስራ ማቆም ወይም መፍረስ ላይ ይወስናል፣

   ሠ) ከሌሎች ማህበራት ጋር ማህበሩን ይቀላቅላል፣

   ረ) የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ይሾማል፣ ያሰናብታል፣ ጥቅማጥቅማቸውን ይወስናል፣

   ሰ) የግዴታ ውል ጉዳዮች ላይ ይወስናል፣

   ሸ) የሂሳብ ሚዛን መግለጫዎችን፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የኦዲተር ዘገባዎችን ያጸድቃል፣

   ቀ) የማህበሩን ኦዲተሮች ይሾማል፣ የስራ ጊዜያቸውን እና ክፍያቸውን ይወስናል፣

2) የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች በስብሰባው ላይ በተገኙ፣ ባልተገኙ፣ በሃሳብ በተለዩ፣ ድምጽ መስጠት ባልቻሉ እና መብታቸውን ባጡ ባለአክሲዮኖች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፣

3) ማናቸውም ሰው ባለአክሲዮን በመሆኑ ያገኘውን መብት ያለሙሉ ፈቃዱ ሊነጠቅ አይችልም።

አንቀጽ 11

የጠቅላላ ጉባኤ አይነቶች

1) ጠቅላላ ጉባኤዎች መደበኛ ወይም ድንገተኛ ናቸው፣

2) አንድ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሂሳብ ዓመቱ በተዘጋ በ6 (ስድስት) ወራት ጊዜ ውስጥ በየዓመቱ አንድ ጊዜ ይጠራል፣

3) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም አዲተሮች ወይም ቢያንስ የማህበሩን ካፒታል 20% (ሃያ ከመቶ) የሚወክሉ ባለ አክሲዮኖች እንዲጠራ ሲጠይቁ የሂሳብ አመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ሊጠራ ይችላል፣

4) ጠቅላላ ጉባኤዎች አስፈላጊ ሆነ ምቹ ሲሆን በሂሳብ አጣሪዎች ወይም በፍርድ ቤት ዳኛ (መኮንን) ሊጠራ ይችላል፣

5) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በተለይም ከፖሊሲ አውጪዎች፣ ከገንዘብ አስቀማጮች ወይም ከመስራቾች ጥቅም አኳያ ወይም ለአነስተኛ ፋይናንስ ስራው ትክክለኛነት እና መረጋጋት ላይ ለመወያየት እንዲሁም ከማህበሩ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ መፍትሄ ለመስጠት የማህበሩን ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል።

አንቀጽ 12

የጠቅላላ ጉባኤ ማሳወቂያ

1) መደበኛ ወይም ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ማስታወቂያ ስፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ከስብሰባው ቀን 15 (አስራ አምስት) ሙሉ ቀናት በፊት ይታተማል፣

2) የስብሰባው ማስታወቂያ የስብሰባውን አጀንዳዎችን ይይዛል፣

3) የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በአማራጭ በንግድ ህግ አንቀጽ 392 ስር በዝርዝር በተገለጹ የስብሰባ ጥሪ ማሳወቂያ ዘዴዎች ሊከናወን ይችላል።

አንቀጽ 13

ምልአተ ጉባኤ ባለመሙላቱ የሚጠራ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ

1) ምልአተ ጉባኤ ባለመሙላቱ ምክንያት ጠቅላላ ጉባኤ ሳይካሄድ ሲቀር እንደመጀመሪያው ጉባኤ በተመሳሳይ የማሳወቂያ ጊዜ ሁለተኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከ8(ስምንት) ሙሉ ቀናት በፊት ስብሰባ ይጠራል።

2) ሁለተኛው ስብሰባ ምልአተ ጉባኤው መሙላቱ ከግምት ሳይወሰድ ይካሄዳል፣ውሳኔዎችም ድምጽ ተአቅቦዎችንም ሆነ ያልተጸፈባቸውን የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ግምት ውስጥ ሳያስገባ በስብሰባው ላይ በተገኙ ባለአክሲዮኖች አብላጫ ድምጽ ይሰጣል።

አንቀጽ 14

የድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማሳወቂያ

ምልአተ ጉባኤ ሳይሟላ ሲቀር እና ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ማስተላለፍ ሳይችል ሲቀር ካስፈለገ በአንድ ሳምንት ጊዜ ልዩነት ማሳወቂያ ወይም ለባለአክሲዮኖች በተመዘገበ ደብዳቤ በመላክ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። የእነዚህ ስብሰባዎች አብላጫ ድምጽ እና ምልአተ ጉባኤ በንግድ ህግ አንቀጽ 425 እና 428 እንደዚሁም በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 22 መሰረት ይሆናል።

አንቀጽ 15

ድምጽ እና ተወካይ የመሾሚያ ጊዜ

1) ከስብሰባው ዕለት ሶስት(3) ሙሉ ቀናት በፊት የአንደራሴነት ስልጣን ፎርም ተሞልቶ የማህበሩ ዋና መ/ቤት መግባት ይኖርበታል፣

2) የውክልናው አይነት፣የሚገባበት ጊዜ እና ሰዓት በስብሰባው ጥሪ ማሳወቂያው ላይ መገለጽ አለበት፣

3) የተወካዩ ድምጽ የመስጠት መብት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣ መመሪያ መሰረት ይወሰናል።

አንቀጽ 16

በስብሰባ ላይ መገኘት መቆጣጠሪያ ቅጽ

1) እያንዳንዱ ስብሰባ በስብሰባ ላይ የመገኘት መቆጣጠሪያ ቅጽ ሊኖረው ይገባል፤ ይህም ቅጽ በስብሰባው ላይ እራሳቸው ወይም በተወካይ የተገኙ ባለአክሲዮኖች ስም፣አድራሻ እና ባለአክሲዮኖቹ የያዟቸው አክሲዮኖች ብዛት ማሳየት አለበት።

2) የመመዝገቢያው ቅጽ በባለአክሲዮኖች ወይም በተወካዮቻቸው ተፈርሞበት በስብሰባው ጽህፈት ቤት ትክክለኛነቱ ይረጋገጣል።

አንቀጽ 17

የጥቅም ግጭት

1) እራሱን ወይም ሶስተኛ ወገንን ወክሎ የሚንቀሳቀስ ባለአክሲዮን ጥቅሞች ከማህበሩ ጥቅም ጋራ ከተጋጨ እንዲህ አይነቱ ባለአክሲዮን ከእንዲህ አይነት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ድምጽ የመስጠት መብቱን አይጠቀምም፣

2) ዳይሬክተሮች ስለ እራሳቸው መብት እና ግዴታ በተያያዘ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ድምጽ አይሰጡም፣

3) በዚህ አንቀጽ መሰረት ድምጽ የመስጠት መብታቸው የተገደቡ አክሲዮኖች ምልአተ ጉባኤ በሚቆጠርበት ጊዜ ግምት ውስጥ ይገባሉ፣

4) ቀደም ሲል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከ1-3 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በባለአክሲዮኖች ስበሰባ ላይ ድምጽ የመስጠት መብት የሚከለክል የትኛውም ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንም።

አንቀጽ 18

ቃለ ጉባኤዎች

1) የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባኤዎች በቃለ ጉባኤ መመዝገቢያ መዝገብ ይመዘገባሉ፤ በቢሮው አብላጫ አባላት ተፈርሞባቸው ትክክለኛነታቸው በሊቀ መንበሩ ወይም በሁለት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ይረጋገጣሉ፣

2) የአንድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ የሚከተሉትን ይይዛል፦

   1) ስብሰባው የተጠራበት ሁኔታ፣
   2) የስብሰባው ቦታ እና ቀን፣
   3) አጀንዳ፣
   4) የጽህፈት ቤቱ አባላት፣
   5) በስብሰባው የተገኙ አክሲዮኖች ብዛት እና ምልአተ ጉባኤ፣
   6) ለስብሰባው የቀረቡ ሰነዶች፣

7) የውይይቶች ማጠቃለያ፣

8) የተሰጡ ድምጾች ውጤቶች፣ እና

9) የተላለፉ ውሳኔዎች ማጠቃለያ።

3) ምልአተ ጉባኤ በማይጠበቅበት ጊዜ ሊቀመንበሩ ይህንን አውነታ በቃለ ጉባኤው ላይ አንዲመዘገብ ያደርጋል፣

4) የቃለ ጉባኤዎቹ ግልባጮች ወይም ከዚያ የተቀዱ ሃሳበ ጉዳዮች በዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በሁለት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ይረጋገጣሉ።

አንቀጽ 19

በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከናወኑ ስራዎች

1) የማህበሩ የሂሳብ ሚዛን፣የትርፍ እና ኪሳራ ሂሳብ እና የዳይሬክተሮች እና የአዲተሮች ዘገባዎች በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ይነበባሉ፤ የተጠቀሰው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ያለፈውን የሂሳብ አመት ዘገባዎች ሊያጸድቅ ወይም ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፤ የዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አስፈላጊ ሲሆን የትርፍ ክፍፍል አመዳደብ እና ስርጭት ላይ እና ከባለፈው የሂሳብ አመት መዛግብት ላይ የሚነሱ ማናቸውም ጥያቄዎች ላይ ውሳኔን ይሰጣል፣

2) አንድ ጠቅላላ መደበኛ ጉባኤ ዳይሬክተሮችን እና አዲተሮችን ሊሾም ወይም ሊሽር፣ ጥቅማ ጥቅሞቻቸው ላይ ይወስናል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሊያሻሽል ይችላል፤ በንግድ ህጉ አንቀጽ 375 መሰረት የአዲተሮች ዘገባ ካደመጠ በኋላ በሂሳቦች፣ የሚከፈሉ ግዴታዎች ላይም ሆነ ከዚያ ጋር የተያያዙ ዋስትናዎችን ያጸድቃል፤ እንዲሁም ለድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከተሰጡት በስተቀር በሌሎች ሁሉም ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

አንቀጽ 20

የመደበኛ እና ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤዎች

የምልዓተ ጉባኤ እና የድምጽ አሰጣጥ መስፈርቶች

1) አንድ መደበኛ ወይም ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ምልአተ ጉባኤ ወይም አብላጫ ድምጽ ካልሞላ ሀጋዊ ውሳኔዎች ማስተላለፍ አይችልም፣

2) በመደበኛ እና ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤዎች ላይ ምልአተ ጉባኤ የአነስተኛ የባለአክሲዮኖች ቁጥር ግምት ውስጥ ገብቶ ከጠቅላላ ካፒታሉ ላይ ድምጽ ተአቅቦዎች፣ ባዶ ድምጽ መስጫዎች፣ እና በህግ፣ በመመስረቻ ጽሁፍ እና በመተዳደሪያ ደንቡ ድምጽ የመስጠት መብታቸውን የተነፈጉ አክሲዮኖች ተቀንሰው ይሰላል፣

3) አንድ ባለአክሲዮን በአንድ መደበኛ ወይም ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ወክሎት እንዲገኝ 1 (አንድ) ተወካይ ብቻ በጽሁፍ ይወክላል።

አንቀጽ 21

በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤዎች ላይ ድምጽ አሰጣጥ እና ውሳኔዎች

1) መጀመሪያ ጊዜ የተጠራ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው ባለአክሲዮኖች መካከል ቢያንስ 25% (ሃያ አምስት ከመቶ) የሚሆኑት ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው ካልተገኙ በስተቀር ውሳኔዎች አይተላለፉም። ምልአተ ጉባኤ ካልሞላ ሁለተኛ ስብሰባ ይጠራል፣

2) ለሁለተኛ ጊዜ ሲጠራ በስብሰባው የተገኙ ድምጽ የሚሰጡ አክሲዮኖች ብዛት ከግምት ሳይገባ ስብሰባው ተካሂዶ ውሳኔዎች ይተላለፋሉ፣

3) በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤዎች ውሳኔዎች ቀሪዎች እና ባዶ ድምጽ መስጫዎች (ካሉ) ተጥለው በአብላጫ ድምጽ ይወሰናሉ።

አንቀጽ 22

የድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤዎች ላይ ድምጽ አሰጣጥ እና ውሳኔዎች

1) የማህበሩን ዜግነት የመለወጥ ወይም ባለአክሲዮኖች ኢንቨስትመንታቸውን በማህበሩ ውስጥ እንዲጨምሩ ለመጠየቅ የሚደረጉ ውሳኔዎች ሁሉም ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው ባለ አክሲዮኖች በሙሉ ወይም በተወካዮቻቸው አማካይነት ተገኝተው በአንድ ድምጽ ሲወሰኑ ነው።

2) በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ድምጽ መስጠት እና ውሳኔዎች ለማስተላለፍ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ከተጠቀሰው በስተቀር 2/3 (ሁለት ሶስተኛ) አብላጫ ድምጽ የሚወሰኑት፣

   ሀ) በመጀመሪያው ስብሰባ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው ወይም ወኪሎቻቸው ከ1/2 (አንድ ሁለተኛ) ያላነሰ ከተገኙ፣

   ለ) በሁለተኛው ስብሰባ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው ወይም ወኪሎቻቸው ከ1/3 (አንድ ሶስተኛ) ያላነሰ ከተገኙ፣

   ሐ) በሶስተኛው ስብሰባ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው ወይም ወኪሎቻቸው ከ1/10 (አንድ አስረኛ) ያላነሰ ከተገኙ፣

አንቀጽ 23

የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች የተፈጸሚነት ወሰን

1) በህግ እና በመመስረቻ ጽሁፉ ወይም መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተወሰኑ የመደበኛ ወይም ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች ቀሪ በሆኑ ወይም በሃሳብ በተለዩ ባለአክሲዮኖች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናሉ፣

2) ከህግ፣ከመመስረቻ ጽሁፉ ወይም ከመተዳደሪያ ደንቡ በተቃራኒ የተወሰኑ የመደበኛ ወይም ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች ከተወሰኑበት ዕለት ጀምሮ በ3 (ሶስት) ወራት ውስጥ ተቃውሞ ሊቀርብባቸው ይችላል። ውሳኔዎችን ውድቅ ለማድረግ የሚቀርቡ ማናቸውም ማመልከቻዎች በንግድ ህጉ አንቀጽ 416 (3)፣ (4) እና (5) ድንጋጌዎች ይገዛሉ፣

3) ውሳኔዎች በሚተገበሩበት ጊዜ በቅን ልቦና የተገኙ የሶስተኛ ወገኖች መብቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ምክንያት አይነኩም።

ምዕራፍ 4

የማህበሩ ስራ አመራር

አንቀጽ 24

የዳይሬክተሮች ሹመት

የዳይሬክተሮችን እድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ልምድ፣ እውቀት እና ዳግም ምርጫ በተመለከተ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1) ማህበሩ 9(ዘጠኝ) አባላት ባሉት እና በማህበሩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሚሾም የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመራል፣

2) ዳይሬክተሮቹ ለ3 (ሶስት) አመታት እንዲያገለግሉ በየ3 (ሶስት) አመታት ይሾማሉ፣

3) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ቦርዱ እንዲቀጥል ከፈለጉ ለአንድ የአገልግሎት ዘመን ብቻ ከሚሰናበቱት የቦርድ አባላት መካከል በቢበዛ አንድ ሶስተኛ በድጋሚ ሊመርጡ ይችላሉ፣

4) ጠቅላላ ጉባኤው በህጉ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች መሰረት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የተሾሙበት የ3 (ሶስት) ዓመት ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ለመሻር እና በምትክ አዲስ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ማካሄድ ይችላል።

አንቀጽ 25

በዋስትና ስለሚያዙ አክሲዮኖች

ዳይሬክተሮች እያንዳንዳቸው ኃላፊነታቸውን እና ተግባራቸውን በትክክል እና በአግባቡ ለመወጣታቸው ዋስትና በማህበሩ ውስጥ 10% (አስር ከመቶ) በስማቸው የተመዘገቡ አክሲዮኖችን ያስይዛሉ፤በዋስትና ያስያዙዋቸዉ አክሲዮኖች ዳይሬክተሩ የማህበሩ የቦርዱ አባል መሆኑ እስኪያበቃ እና ለማህበሩ ተጠያቂነቶቹ ሙሉ በሙሉ ቀሪ እስኪሆኑ ድረስ አይለቀቁም።

አንቀጽ 26

የዳይሬክተሮች ምዝገባ

1) ማህበሩ የዳይሬክተሮችን የጋብቻ ሁኔታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ሙያ፣ልምድ እና በሌላ ተቋም ውስጥ ዳይሬክተርነት ደረጃ የመሳሰሉ ዝርዝሮችን የያዘ የዳይሬክተሮች መዝገብ በዋና ጽ/ቤቱ ይይዛል፣

2) በመዝገብ የገቡ ዝርዝር ሁኔታዎች በሙሉ እና በውስጡ ያሉ ሌሎች ማሻሻያዎች ሁሉ በመዝገቡ ውስጥ ከተመዘገቡ ወይም ከተሻሻሉ በ15 (አስራ አምስት) ቀናት ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይላካሉ።

አንቀጽ 27

የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣን እና ተግባር

የዳይሬክተሮች ቦርድ አግባብነት ባላቸው ህጎች፣ በመመስረቻ ጽሁፉ እና በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ እንደዚሁም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሚተላለፉ ውሳኔዎች ስልጣን እና ተግባራቸው ይወሰናል።

አንቀጽ 28

የዳይሬክተሮች ተጠያቂነት

1) ዳይሬክተሮች በህግ፣ በመመስረቻ ጽሁፉ ወይም በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ እና በስብሰባዎች በሚሰጡ ውሳኔዎች የሚሰጣቸውን ተግባራት ከአንድ ወኪል በሚጠበቅ ጥንቃቄ የማከናወን ኃላፊነት አለባቸው፣

2) ዳይሬክተሮች ተግባራቸውን ማከናወን ባለመቻል የሚፈጠር ጉዳት ለማህበሩ በጋራ እና በተናጠል ተጠያቂ ናቸው፣

3) በጋራ እና በተናጠል ተጠያቂ የሚሆኑት ዳይሬክተሮች ከጠቅላላ ስራ አመራር ጋር በተያያዘ በጥንቃቄ የመስራት አጠቃላይ ኃላፊነት አለባቸው፣

4) ዳይሬክተሮች ባላቸው ስልጣን እና እውቀት መውሰድ የሚገባቸውን እርምጃ በመውሰድ ማህበሩን ተጠያቂ እንዳይሆን ወይም ተጠያቂነቱን ለመቀነስ ሳይችሉ ከቀሩ በጋራ እና በተናጠል ይጠየቃሉ።

አንቀጽ 29

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር

1) የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ከአባላቱ መካከል በአጠቃላይ በቦርዱ አብላጫ ድምጽ ይመረጣል፣

2) የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ወይም እሱ በማይኖርበት ጊዜ ቀደምትነት ያለው ዳይሬክተር ስብሰባዎችን ይመራል። ሁለቱም ሰዎች በማይኖሩበት ጊዜ በጉባኤው የተሾመ ዳይሬክተር ስብሰባውን ይመራል፣

3) ሊቀመንበሩ በማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ወይም ሊቀመንበሩ በሚወስነው ሌላ የትኛውም ቦታ የሚካሄድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ የመጥራት ስልጣን አለው፣

4) የዳይሬክተሮች ቦርድ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብ እና የንግድ ህጉ መሰረት ስብሰባዎችን የሚመራበት የስብሰባ ስርዓተ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ 30

የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ

1) 51% (ሃምሳ አንድ ከመቶ) የሚሆኑት የዳይሬክተሮች ወይም ወኪላቸው ካልተገኙ በስተቀር የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ማሳለፍ አይችልም። ውሳኔዎች በአብላጫ ድምጽ ይተላለፋሉ፣

2) አንድ ዳይሬክተር ከቀረ በዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ መሳተፍ የሚችለው በሌላ ተወካይ ዳይሬክተር አማካኝነት ብቻ ይገኛል፣

3) የቦርዱ ውሳኔ በቃለ ጉባኤ ተይዞ በስብሰባው ላይ በተገኙ ዳይሬክተሮች መፈረም አለበት፣ ቃለ ጉባኤዎች በቃለ ጉባኤ መያዣ መዝገብ ውስጥ ይቀመጣሉ፣

4) የውሳኔ ግልባጮች በሊቀመንበሩ እና በጸሐፊው ተረጋግጠው ይፈረምባቸዋል።

አንቀጽ 31

ዳይሬክተሮችን መተካት

1) የዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 24 (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሂሳብ አመቱ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮች ቢለቁ ቀሪዎቹ ዳይሬክተሮች ለቃቂ ዳይሬክተሮች የተሾሙበት ጊዜ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሌሎች ሰዎችን ሊሾሙ ይችላሉ፣

2) ሹመታቸው እንዲጸድቅ ለሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ መቅረብ አለበት፣ ጠቅላላ ጉባኤው ሹመታቸውን ያጸድቃል ወይም በእነሱ ምትክ ሌሎች ዳይሬክተሮችን ይሾማል። የእነዚህ ሰዎች ሹመት በጠቅላላ ጉባኤው ባይጸድቅም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በተሾሙ ሰዎች የተከናወነ ድርጊት ዋጋ ያለው ነው፣

3) በየትኛውም ጊዜ የዳይሬክተሮቹ ቁጥር ከግማሽ ካነሰ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተግባራትን ለማከናወን ካልተቻለ ቦታቸውን በለቀቁ ዳይሬክተሮች ምትክ አዲስ ዳይሬክተሮችን እንዲሾም የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ይጠራል፣

4) የማህበሩ ዳይሬክተሮች በማናቸውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሊሻሩ ይችላሉ፣

5) የአንድ ዳይሬክተር ከሹመቱ የሚነሳው፦

   ሀ. የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ከሆነ ሲከስር ወይም ኪሳራ ውስጥ ሲገባ፣ ወይም በአበዳሪዎቹ ሲዋጥ፣

   ለ. አዕምሮው ሲታወክ፣

   ሐ. በዳይሬክተሮች ቦርድ የአሰራር ሂደት ደንብ ውስጥ በተጠቀሱ በማናቸውም ምክንያቶች፣

   መ. በአነስተኛ የፋይናንስ ስራ ሰዋድ ቁጥር 626/2001 እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መስፈርት ማሟላት ሳይችል ሲቀር ነው፣

   ሠ. ጠቅላላ ጉባኤው በማንኛውም ጊዜ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ከሃላፊነታቸው የማንሳት ሥልጣን አለው።

አንቀጽ 32

የማህበሩ ዋና ስራ አስፈጻሚ ስልጣን እና ተግባር

1) ዋና ስራ አስፈጻሚው የማህበሩ ስራ አመራር የበላይ ኃላፊ እና ለአጠቃላይ አስተዳደሩ ኃላፊነት አለበት።

2) ከላይ የተጠቀሰው ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ስራ አስፈጻሚው የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በመመስረቻ ጽሁፉ ለተደነገጉ ዓላማዎች መሳካት በማህበሩ ስም መስራት፣
2. በሁሉም መንግስታዊ ፣ የግል ተቋማት፣ ባንኮች እና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ዘንድ በአለማቀፍ እና የሀገር ውስጥ ስራዎች ላይ ማህበሩን ወክሎ የመገኘት፣
3. የማህበሩን ደንቦች እና መመሪያዎች በማርቀቅ የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲያጸድቃቸው ማቅረብ፣
4. የማህበሩን ሂሳቦች አያያዝ የመምራት እና የመቆጣጠር፣
5. የስራ አመራር መደበኛ ስብሰባዎችን መጥራት እና የማህበሩን የእለት ተዕለት ስራዎች የማከናወን፣
6. የመጠባበቂያ ሂሳብ በህግ ፣ በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ የተቀመጡ እና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚጸድቁ ሌሎች መጠባበቂያ ገንዘቦችን ማደራጀት፣
7. በመመስረቻ ጽሁፉ እና በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ ወይም በዳይሬክተሮች ቦርድ የተሰጠውን ስልጣን ለማህበሩ ስራ መቀላጠፍ ለሌላ የማህበሩ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ መወከል፣
8. ወኪሎችን፣የህግ አማካሪ ወይም ሌላ ባለሙያ ለማህበሩ ጥቅም የመሾም ወይም የማሰናበት፣
9. ቦርዱን አስቀድሞ በማሳወቅ በማህበሩ ስም በየትኛውም ባንክ ወይም ባንኮች ተንቀሳቃሽ ሂሳቦች መክፈት እና መያዝ፣
10. ሁሉም ድራፍቶች፣ ቼኮች፣ የግብይት ሰነዶች፣ የቃል ኪዳን ማስታወሻዎች እና ሌሎች የስምምነት እና የተስፋ ሰነዶች የመቀበል፣ የመስጠት፣ የመፈጸም፣ የመፈረም፣ የመቀነስ እና የማስገቢያ እና የመላኪያ ዲክላራሲዮኖችን ሁሉ መፈረም፣
11. ቦርዱን በማሳወቅ በየትኛውም የኢንሹራንስ ኩባንያ ወይም ግለሰብ ዘንድ የኪሳራ፣ የጉዳት፣ የአደጋ፣ የስጋት እና የየትኛውም ተጠያቂነት መድን ስለማህበሩ መግባት፣
12. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስቀድሞ ሲወስን ትርፍ ገንዘቦችን በማህበሩ ዓላማዎች ወሰን ውስጥ ስራ ላይ ማዋል።

3) በተጨማሪም ስራ አስፈጻሚው፦

ሀ. የሂሳብ ሚዛን ፣ የትርፍ እና ኪሳራ በየሂሳብ አመቱ መጨረሻ ማዘጋጀት፣

ለ. የባለፈውን ዓመት ዘገባዎች እና የማህበሩን ስራ እንቅስቃሴዎች የማቅረብ፣

ሐ. በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፉ እና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ማናቸውንም ማሻሻያ ሃሳቦች ለዳይሬክተሮች ቦርድ ማቅረብ፣

መ. ለሁሉም ህጋዊ ወጪዎች፣ ክፍያዎች እና ለማህበሩ እድገት፣ ስራ እና ምዝገባ አስፈላጊ የሆኑ የወጪ ክፍያዎችን ማጽደቅ፣

ሠ. በዚህ ውስጥ በግልጽ ያልተጠቀሱ ግን ደግሞ ለማህበሩ ዓላማ መሳካት አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውም ነገሮች የማከናወን ኃላፊነት አለበት።

ምዕራፍ 5

የሂሳብ እና ተያያዥ እንቅስቃሴዎች አያያዝ

አንቀጽ 33

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

የአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 እና በንግድ ህጉ ከሂሳብ እና መዝገብ አያያዝ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ድንጋጌዎች በማህበሩም ሂሳቦች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 34

የሂሳብ መዛግብት እና መረጃ

ማህበሩ ስለ እንቅስቃሴዎች እና ግብይቶች በግልጽ እና በትክክል ለማሳየት እና ስለግብይቱ አጠቃላይ ገፅታን ለማሳየት ጠቃሚ የሆኑ የሂሳብ መረጃዎችን በአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 ድንጋጌዎች መሰረት የፋይናንስ አቋሙን ለማብራራት አስፈላጊ የሆኑ መዛግብትን ይይዛል።

አንቀጽ 35

የሂሳብ ዓመት እና የፋይናንስ ዘገባ

1) የማህበሩ የሂሳብ ዓመት እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1 ቀን ጀምሮ በቀጣዩ ዓመት ጁን 30 ቀን ይጠናቀቃል። ሆኖም የመጀመሪያው የሂሳብ ዓመት ማህበሩ ከተመዘገበበት አስት አንስቶ እ.ኤ.አ. ጁን 30 ቀን 2018 ይጠናቀቃል፣

2) በእያንዳንዱ የሂሳብ አመት መጨረሻ ከላይ በአንቀጽ 32 (3) በቀረበው ዘገባ መሰረት የዳይሬክተሮች ቦርድ በማህበሩ አጠቃላይ አሰራር ላይ ጠቅላላ ዘገባ አዘጋጅቶ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣

3) ዘገባው በትርፍ እና ኪሳራ ሂሳብ ላይ፣ በዳይሬክተሮች እና ኦዲተሮች ጥቅማ ጥቅም ላይ ዝርዝር መረጃ እና በመጠባበቂያዎች አመዳደብ እና የትርፍ ክፍፍል ላይ ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፣

አንቀጽ 36

ሂሳብ እና ዘገባ ለኦዲተሮች ማቅረብ

የዳይሬክተሮች ዘገባ፣ የቆጠራ ውጤት፣ የሂሳብ ሚዛን መግለጫ እና የትርፍ እና ኪሳራ ሂሳብ እና የዳይሬክተሮችን ዘገባ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ዓመታዊ ጉባኤ ጥሪ ከመተላለፉ ከ45 (አርባ አምስት) ቀናት በፊት በማህበሩ ዋና ስራ አስፈጻሚ ለኦዲተሮች ይቀርባል።

አንቀጽ 37

የሂሳብ ሚዛን፣ትርፍ እና ኪሳራ ሂሳብ አዘገጃጀት

ከዚህ በታች በአንቀጽ 40 ላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሂሳብ ሚዛን ፣ የትርፍ እና ኪሳራ ሂሳብ፣ የእርጅና ቅናሽ ሂሳቦች ዝግጅት ለንግድ ህጉ፣ ለአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001፣ ለሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች እና ለሂሳብ መርሆች ድንጋጌዎች ተገዥ ይሆናሉ፣

አንቀጽ 38

የኦዲተሮች ሹመት እና ተግባር

1) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማረጋገጫ እንደተጠበቀ ሆኖ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ኦዲተሮችን ይሾማል፣

2) የተሾሙት ኦዲተሮች ለሶስት አመታት በስራ ላይ ይቆያሉ፣

3) ኦዲተሮች ስራቸውን የሚያከናውኑበት ጊዜ ንብረት እና እዳዎችን አመዘጋገብ በሚመለከት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያስቀመጣቸውን ዝቅተኛ የኦዲት መስፈርቶችን መጠበቅ አለባቸው፣

4) የኦዲተሮች ዘገባ የማህበሩ የሂሳብ አመት ካበቃ በኋላ ከ90 (ዘጠና) ቀናት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መላክ አለበት፣

5) ኦዲተሮች በንግድ ህጉ አንቀጽ 368 እስከ 380፣ በአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ 626/2001 እና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ስራቸውን ማከናወን አለባቸው።

አንቀጽ 39

ካፒታል እና ህጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብ አያያዝ

ማህበሩ አግባብነት ባላቸው ህጎች እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች መሰረት ካፒታሉን እና ህጋዊ መጠባበቂያውን መያዝ አለበት፣

አንቀጽ 40

ገንዘቦች፣የእርጅና ቅናሾች ሂሳብ አያያዝ

1) ማህበሩ አግባብነት ባላቸው ህጎች እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች መሰረት ገንዘቦችን መያዝ አለበት፣

2) ማህበሩ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ለንብረቶቹ ቅንሰት እና ለካፒታል ወጪው እየተከፈለ የሚያልቅ ሂሳብ መያዝ አለበት።

አንቀጽ 41

የትርፍ አመዳደብ እና ክፍፍል

1) የዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከተጣራ ትርፍ ላይ ለባለአክሲዮኖች የትርፍ ክፍፍል ሃሳብ በዳይሬክተሮች ቦርድ ሲቀርብ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ይጸድቃል። የትርፍ ክፍፍሉ ህጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብ እና በዳይሬክተሮች ቦርድ ቀርቦ ከጊዜ ወደ ጊዜ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሚያፀድቀው መሰረት ሌሎች የመጠባበቂያ ገንዘቦች ከተቀነሱ በኋላ ይከናወናል። ከላይ የተጠቀሱት የትርፍ ክፍፍሎች በሌላ አኳኋን በህግ ካልተገለጸ በስተቀር በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት ለባለአክሲዮኖች ይከፋፈላል፣

2) የትርፍ ክፍፍሎች እወጃ በገንዘብ ወይም በአክሲዮኖች ሊከፈል ይችላል፣

3) ከጸደቀው የሂሳብ ሚዛን በተቃራኒ የተከፈሉ የትርፍ ክፍፍሎች ልክ እንደተጭበረበሩ ይቆጠራል፣ በወንጀል እና በፍትሐብሔር ተጠያቂ ያደርጋሉ፣

4) የክፍያው ቀን እና ሁኔታ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ መወሰን አለበት።

አንቀጽ 42

የሂሳብ መግለጫዎች ይፋ ማድረግ

1) ማህበሩ በየሩብ አመቱ፣ የሩብ አመቱ እንዳለቀ በአራት ሳምንት ውስጥ የተፈረመበት የሂሳብ ሚዛን መግለጫ፣የትርፍ እና ኪሳራ ሂሳብ መግለጫ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መላክ አለበት፣

2) የማህበሩ አዲት የተደረገ የሂሳብ ሚዛን፣ የትርፍ እና ኪሳራ ሂሳብ መግለጫ በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት በሚሰራጭ ጋዜጣ ላይ መታተም አለበት።

ምእራፍ 6

ስለሞግዚት አስተዳደር፣መፍረስ እና ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 43

ስለማህበሩ ሞግዚት አስተዳደር እና መፍረስ

1) የአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 ድንጋጌዎች በማህበሩ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፣

2) በአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 አንቀጽ 19 ስር ከተጠቀሱት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሁኔታዎች መከሰት በሞግዚት አስተዳደር ማህበሩ ስር እንዲመደብ በቂ ምክንያት ይሆናሉ፣

3) ከአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 ጋር አስካልተቃረነ ድረስ ማህበሩ በሞግዚት አስተዳደር ስር መሆኑ እና ከመፍረሱ ጋር በተያያዘ የንግድ ህጉ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 44

የመመስረቻ ጽሁፉ እና የመተዳደሪያ ደንቡ መሻሻል

1) በህግ ካልተጠቀሰ በስተቀር የማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ እና ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሊሻሻል ይችላል፣

2) በመመስረቻ ጽሁፉ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሻሻል ላይ ድምጽ እንዲሰጥ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከተጠራ በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ፣ በንግድ ህጉ እና በአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 ድንጋጌዎች መሰረት ጉባኤው ስራውን ማከናወን አለበት።

አንቀጽ 45

የሌሎች ህጎች ተፈጻሚነት

የንግድ ህጉ እና የአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ ባልተካተቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 46

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1) በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ በአማርኛው እና በእንግሊዘኛ ቋንቋው መካከል የትርጉም ልዩነት ቢኖር የአማርኛው ትርጉም ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

2) ይህ የመተዳደሪያ ደንብ ጠቅላላ ጉባኤው ከፈረመበት በኋላ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ኤጀንሲ ተረጋግጦ ከተመዘገበ እና ከጸደቀ በኋላ ተፈጻሚ ይሆናል።

ዛሬ በቀን _____ በ _____ ወር 200___ ዓ.ም አዲስ አበባ ውስጥ ተዘጋጅቶ ተፈረመ።

የማህበሩ መስራች ባለአክሲዮኖች ስም፣ ፊርማ እና አድራሻ

ተ.ቁ	የባለአክሲዮኖች ሙሉ ስም	ዜግነት	አድራሻ					የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት	የአንዱ የአክሲዮን ዋጋ (በብር)	ጠቅላላ የተፈረመ አክሲዮኖች ዋጋ (በብር)	የተከፈለ አክሲዮኖች ብዛት	ያልተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት	ፊርማ	ቀን
			ክተማ	ክ/ከተማ	ቀበሌ (ወረዳ)	የቤት ቁጥር	ስልክ ቁጥር							
1	አቶ ክፍሌ ብርሃኑ ወንድሙ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ቦሌ	03	23/1065	0911206600	2,000	1000	2,000,000	2,000			
2	አቶ ደጀኔ ወ/ማርያም በንቲ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	የካ	13	አዲስ	0911203019	3,000	1000	3,000,000	2,900	100		17/11/05
3	ወ/ሮ አለምፀሐይ አለሙ ባቦ	ኢትዮጵያዊት	አ.አ	ንፋስ/ ሳፍቶ	02	አዲስ	0911248157	300	1000	300,000	300			
4	አቶ ፍቅሬ ዘውዴ ደጋጋ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	የካ	13	B553-18	0912506853	700	1000	700,000	400	300		
5	አቶ ሳሙኤል ተስፋዬ ታደሰ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ንፋስ/ ሳፍቶ	01	አዲስ	0911209085	300	1000	300,000	150	150		
6	ወ/ሮ ወርቅነሽ መኮንን ጎንጥ	ኢትዮጵያት	አ.አ	የካ	02	MH39	0921778572	300	1000	300,000	300			
7	ወ/ሮ ዶኔክ ተስፋዬ ዘሞ	ኢትዮጵያዊት	አ.አ	የካ	08	870	0911214654	250	1000	250,000	250			
8	ወ/ሮ ሙሉ ጎበና ተሊላ	ኢትዮጵያዊት	አ.አ	ቦሌ	12	New	0921627774	100	1000	100,000	100			
9	አቶ ማይክል መንገሻ ደሰሉ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	አራዳ	01	395	0911516040	200	1000	200,000	100	100		
10	አቶ አፈወርቅ ዮሐንስ ገርማሞ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ንፋስ/ ሳፍቶ	01	አዲስ	0911242303	250	1000	250,000	100	150		17/11/2005
11	ወ/ሮ ራሔል አክሰወልድ ገ/ስላሴ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	አራዳ	11/12-03	1163	0911683737	300	1000	300,000	200	100		
12	አቶ ወሰን አስፋው ቅጤሳ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ክ/ቀራንዮ	08	1904	0911206186	500	1000	500,000	500			
13	አቶ ቴምድሮስ አብርሃም ሀብተሚካኤል	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ቦሌ/ldc	02	062	0911200325	1,000	1000	1,000,000	500	500		
14	አቶ ጋረደው አሰፋ ማሞ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ንፋስ/ ሳፍቶ	12	1208	0911665920	150	1000	150,000	100	50		

ተ.ቁ	የባለአክሲዮኖች ሙሉ ስም	ዜግነት	አድራሻ					የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት	የአንዱ የአክሲዮን ዋጋ (በብር)	ጠቅላላ የተፈረሙ አክሲዮኖች ዋጋ (በብር)	የተከፈለ አክሲዮኖች ብዛት	ያልተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት	ፊርማ	ቀን
			ክተማ	ክ/ክተማ	ቀበሌ (ወረዳ)	የቤት ቁጥር	ስልክ ቁጥር							
15	አምባዬ አጋቶ አናታ (ዶ/ር)	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ቦሌ	6	155	0924849898	100	1000	100,000	100			
16	የኔነሕ ሙሉጌታ ደነቀ (ዶ/ር)	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ንፋስ/ ላፍቶ	12	አዲስ	0911542854	100	1000	100,000	100			
17	አቶ ጌታቸው ማሞ አረዳ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ንፋስ/ ላፍቶ	1	አዲስ	0911642573	200	1000	200,000	100	100		
18	አቶ ያዕቆብ ኢሣያስ ኪዳኔ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	አራዳ	7	498/ለ	0911903061	100	1000	100,000	100			
19	አቶ ገበየሁ አበራ አየለ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ንፋስ/ ላፍቶ	4	1507	0925273468	100	1000	100,000	100			
20	አቶ ጌታሁን ካሣዬ መኩሪያ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ቂርቆስ	8	247	0913853776	100	1000	100,000	100			
21	አቶ ምስጋና መኩሪያ ዱራ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ንፋስ/ ላፍቶ	4	433	0911424992	100	1000	100,000	100			
22	አቶ አብዲ በቀለ ሀይሉ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ጉለሌ	07	962	0923992346 0911448996	100	1000	100,000	100			
23	አቶ ይገረም ካሣ አባከሀ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ቦሌ	11	B11/30	0911677459	100	1000	100,000	100			
24	አቶ አስናቀ አማኑኤል አያሌ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ቦሌ	03	19/271	0943044503	250	1000	250,000	250			
25	ሰማ ደገፋ ጉደታ (ዶ/ር)	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ቦሌ	03	2032	0912625778	300	1000	300,000	200	100		
26	ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ	ቦሌ	03	2185	0116185105	1,000	1000	1,000,000	1000			
27	ወ/ሮ ትዝታ ክተማ ወዴሳ	ኢትዮጵያዊት	አ.አ	ቦሌ	01	አዲስ	0911632399	100	1000	100,000	100			

በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ ቅርንጫፍ (12)
ቁጥር ቅ/12/1824ህ/10
በጽ/ቤታችን በአቶ ቀርቦው ፈርመዋል ::
አዲስ አበባ 25/11 ቀን 20 09 ዓ.ም

ሠ/ ሳራ ሀይሉ ጠ/ፃዲቅ
SARA HAILU W/TSADIK
ከፍተኛ የሰነዶች ማረጋገጥ
ባለሙያ I
Senior Documents Authentication Expert I



በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ
ቅርንጫፍ (12)

የተከፈለበት ምክንያት
የገንዘቡ መጠን 777
በፈቃዱ
ወደ ውጭ ሀገር
የደረሰኝ ቁጥር 582490
25-11 ቀን 20 09
የተመዘገበ ቀረጥ መሰብሰቢያ ኦፊሰሩ
ስም
ፊርማ